## የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የምግብ ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ

ግንቦት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## Contents


1. መግቢያ ..... 3

ክፍል አንድ ..... 4

ጠቅላላ ..... 4

2. አጭር ርዕስ ..... 4

3. ትርጓሜ ..... 4

4. ዓላማ ..... 5

5. የተፈፃሚነት ወሰን ..... 5

ክፍል ሁለት ..... 6

ምግብ ስለ መመዝገብ ..... 6

6. አጠቃላይ ..... 6

7. የአመዘጋገብ ሂደት፣ እድሳትና ለውጥ ሁኔታ ..... 6

8. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦች ስለመመዝገብ ..... 7

9. በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምግቦችን ስለመመዝገብ ..... 8

10. ስለ ቅድመ ማሳወቅ ..... 10

11. የምዝገባ ለውጥ፣ ዳግም ምዝገባና እድሳት ሁኔታ ..... 10

12. ምግብ ስለ ማስተዋወቅ ..... 11

13. ስለ አስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድ ..... 11

14. ቅሬታ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ስርዓት ..... 11

15. ተፈጻሚት የማይኖራቸው ህጎች ..... 11

16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ..... 11

17.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ..... 11

## 1. መግቢያ

ለህብረተሰቡ የሚቀርቡትን የምግብ አይነቶች ደህንነትና ጥራት ለማረጋገጥ በምግብ ምዝገባና ፈቃድ ላይ ያተኮረ ጠንካራ እና ውጤታማ የምግብ ጥራት እና ደህንነት ቁጥጥር በማስፈለጉ፤

በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦች ለህብረተሰቡ ለምግብነት አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን በማረጋገጥ የገበያ ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ የሚገኙትን የምግብ አይነቶች ዝርዝር ማወቅ በማስፈልጉ፤

በምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 55 (3) እና በምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀጽ 4(1) መሰረት ይህ የምግብ ምዝገባ አፈፃፀም መመርያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የምግብ ምዝገባ አፈፃፀም መመርያ ቁጥር 34/2009” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

በአዋጁና በደንቡ ላይ የተቀመጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. “ምግብ” ማለት በሀገር ውስጥ ወይም በውጪ ሀገ ድርጅት ተመርቶ ለህብረተሰቡ የሚቀርብ እና ዝርዝሩ በዚህ መመሪያ ላይ አባሪ የተደረገ ምርት ነው፡፡
2. “ምግብ አምራች ምግብ በማምረት ከአንድ ክልል በላይ ለገበያ ሽያጭ የሚቀርብ ምግብ የሚያመርት ተቋም ነው፣ ሆኖም ባህላዊ ምግቦችን የሚያዘጋጁ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን አይጨምርም፤
3. “በቅድሚያ የታሸገ ምግብ” ማለት ሻጩ ጋር ከመድረሱ በፊት በምግብ አምራቹ የታሸገ ምርት ነው፡፡
4. “ምዝገባ” ማለት በዚህ መመርያ ላይ ዝርዝራቸው አባሪ በተደረገው መሰረት ምዝገባ የ ለህብረተሰቡ በሽያጭ ከመቅረቡ በፊት እንደ ምግቡ አይነትና ባህሪ የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የሚሰጥ የቅድመ ገበያ ፈቃድ ነው፡፡
5. “ቅድመ ማሳወቅ” ማለት ዝርዝራቸው በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተካተቱ ከውጪ ሀገር የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የምግብ አይነቶች ለህብረተሰቡ ሽያጭ ከመቅረባቸው በፊት ባለሰልጣኑ እንዲያውቅ የማድረግ ሂደት ነው፡፡
6. ”የምግብ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት አምራች ድርጅት የምግቡን ጥራትና ደህንነት በተጠበቀ መልኩ ለማምረት እንዲችል ተግባራዊ የሚያደርጋቸው የአሰራር ሥርዓቶች ሆኖው በባለስልጣን መስሪያቤቱ እውቅና የተሰጣቸው ናቸው፡፡
7. “የሶስተኛ ወገን ብቃት ማረጋገጫ” ማለት የምግቡ አምራች ድርጅት ምግቡ የሀገሪቱ ደረጃ በሚፈቅደው መስፈርት መሰረት ምግብ ለማምረት የሚያስችል ብቃት ያለው ስለመሆኑ ብቃት ባለውና እውቅና በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ የሚሰጥ የእውቅና ነው፡፡
8. “የሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት” ማለት ለምዝገባ የሚቀርበው ምግብ የተቀመጠውን የጥራትና ደህንነት መስፈርት የሚያሟላ ስለመሆኑ እውቅና በተሰጣቸው ላቦራቶሪዎች ተመርምሮ ሲረጋገጥ የሚሰጥ የምግብ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ውጤት ማለት ነው፡፡

9. “በልዩ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውል የምግብ አይነ‹ ሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው ለሚገኙ የውጪ ዜጎች በተወሰነ መጠንና ጊዜ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውል የምግብ አይነት ነው፡፡

10. “በ24 ሠዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል የምግብ አይነት” ማለት ምንም አይነት ተጨማሪ የምግብ ዝግጅት ሂደት የማይደረግባትና በ24 ሰዓት ውስጥ ጥቅም ላይ ካልዋለ ለብልሽት ተጋላጭ የሆነ የምግብ አይነት ማለት ነው፡፡

11. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማ‹ ድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ድርጅት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ፤

12. “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግ መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

13. “አዋጅ” ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አሰተደደርና ቁጥጥር አዋጅ ፃ

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ

1. በሀገራችን የሚረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ እና ከዚህ መመሪያ ጋር ዝርዝራችው አባሪ የተደረጉ ምግቦች ለህብረተሰቡ ምግብነት ከመዋላቸው በፊት ህጋዊ ምንጫቸው ታውቆ ጥራታቸው እና ደህንነታቸው ተረጋግጦ ወደ ገበያ እንዲገቡ ፈቃድ ለመስጠት፣

2. የምግብ ምዝገባ አሰራሮችን ግልጽ በማድረግ የሚሰጡትን አገልግሎቶች ለማሳለጥ፤

3. ለገበያ የሚቀርቡ ምግቦች ህጋዊ ምንጭ እንዲያውቅ በማድረግ ህብረተሰቡ ህጋዊ የሆኑ ምግቦች ህጋዊ ካልሆኑ ምግቦች የሚለይበት በቂ መረጃ እንዲያገኝ እና ህገወጥ የምግብ ንግድ ዝውውር ለመቆጣጣር የሚደረገው እንቅስቃሴ በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን ለማድረግ፣

4. በሕገወጥ ምግብ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጤና ችግር ከወዲሁ ለመከላከል እና የምግብ ደህንነት ችግር ሲያጋጥምም በህብረተሰቡ ላይ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡

## 5. የተፈፃሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ ወይም በውጪ ሀገር ምግብ አምራች ድርጅት ተመርቶ ለህብረተሰቡ የሚቀርብ እና ዝርዝሩ በዚህ መመሪያ ላይ አባሪ የተደረገ ምርት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በጨቅላ፣ የታዳጊ ህፃናት ምግቦች እና ተጨማሪ ምግቦች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ምግብ ስለ መመዝገብ

### 6. አጠቃላይ

1. ለህብረተሰቡ የሚቀርብ እና ዝርዝሩ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገ ማንኛውም ምግብ በባለሥልጣኑ ሳይመዘገብ እና ፈቃድ ሳያገኝ ለሽያጭ ማቅረብ፣ ማስተዋወቅ ወይም የምርት ይዘት፣ አይነትና ሂደት ላይ ለውጥ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

2. ማንኛውም ለምዝገባ የሚቀርብ ምግብ በሀገር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የደህንነት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፡-

   ሀ) ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውሉ ፤

   ለ) ለግለሰብ ጥቅም የሚውሉ ፤

   ሐ) ለሳይንሳዊ ምርምሮች የሚውሉ ፤

   መ) ለተለያዩ ግልጋሎት ለናሙናነት የሚገቡ፤

   ሠ) ለተለያዩ ሆቴሎችና ምግብ አምራች ድርጅቶች እንደ ምርት ግብዓት እና ጥሬ እቃነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ፤

   ረ) በ24 ሠዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ፤

   ሰ) ለተለየ የህብረተሰብ ክፍል በልዩ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውሉ

   ምግቦች ሳይመዘገቡ ለህብረተሰቡ ሽያጭ ሊቀርቡ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

### 7. የአመዘጋገብ ሂደት፣ እድሳትና ለውጥ ሁኔታ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ምግብን ለማስመዝገብ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጠውን ቅፅ አንድ በመሙላት እንደ ቅደም ተከተሉ ለገቢ እና ለሀገር ውስጥ ምግቦች በአንቀፅ 9 እና 10 ላይ የተዘረዘሩ መረጃዎችን በማያያዝ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ለምዝገባ የሚቀርቡ ሰነዶች ሁሉ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚቀርቡ ሲሆን፤ ከእንግሊዘኛ ወይም አማርኛ ውጪ በሆኑ ሌሎች ቋንቋዎች የተዘጋጁ ሰነዶች ከሆኑ ግን የሰነዶቹ ህጋዊ ትርጉም ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. ለምዝገባ የቀረቡት ምርቶች የምግብ ጭማሪ ወይም ምግብን ለማበልጸግ ጥቅም ላይ የሚውል ውህድ ከሆኑ ለተባለው አገልግሎት መዋል ስለመቻላቸው ባለሰልጣኑ ሀገራዊ ወይም አለም አቀፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ያረጋግጣል፡፡

4. ባለስልጣኑ በመመሪያው ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች የተሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ምግቡን በመመዝገብ የምዝገባ ሰርተፊኬት እንደ ቅደም ተከተሉ ለሀገር ውስጥ እና ለገቢ ምግቦች በ 17 ቀን እና 2 ወር ይሰጣል፡፡

5. ማንኛውም አመልካች ምግብን ለማስመዝገብ ከባለስልጣኑ እስከ ሶስት ጊዜ ማብራሪያ ተጠይቆ ተገቢውን ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ በድጋሚ እንደ አዲስ ማመልከት የሚችለው ከሶስት ወር በኋላ ነው፡፡

6. ምግብን በማስመዝገብ የገበያ ፍቃድ ለማግኘት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 370/2008 በወጣው የአግልግሎት ክፍያ ተመን መሰረት ሲሆን ለሰነድ ቅድመ ግምገማ ለመጀመሪያ ጊዜ 350 ብር፣ ለአዲስ ምዝገባ ሰነድ 1650 ብር፣ ለዳግም ምዝገባ 870 ብር፣ ለከፍተኛ የምዝገባ ለውጥ 870 ብርና ለአነስተኛ ምዝገባ ለውጥ 650 ብር ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 8. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦች ስለመመዝገብ

ማንኛውም ዝርዝራቸው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረጉ እና በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማስመዝገብ ፡-

1. በዚህ መመሪያ ላይ በቅፅ አንድ የተያያዘውን ቅፅ መሙላት፤
2. በምርቱ ስሪት ሀገር የምርት ስርጭት ፈቃድን የሚገልጽ ሰርተፊኬት /free sale certificate/፣
3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ስሪት ሀገሩ በምርት ስሪት ሀገር የምርት ስርጪት ፈቃድን የሚገልጽ ሰርተፊኬት /free sale certificate/ የማይሰጥ መሆኑ ከተረጋገጠ የምርት ስሪት ሀገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /certificate of origin/ ማቅረብ ይችላሉ፣
4. በምርት ስሪት ሀገር ተቆጣጣሪ ተቋም ምርቱን ለማምረት ወይም ለምርት ሽያጭ የተሰጠው የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /food manufacturing or product registration certificate or approval/፣
5. ወቅታዊነት ያለው፣ ለምዝገባ የቀረበውን ምርት ለማምረት እውቅና የተሰጠው እና በምርት ስሪት ሀገር ባለ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት የተደረገ ማረጋገጫ (authenticate) የምግቡ አምራች ድርጅት ተግባራዊ ያደረገው የጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት ሰርተፊኬት፣
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ስሪት ሀገር የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት በማይኖርበት ወቅት ይህን ተግባር እንዲሰራ በኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚንስቴር በኩል ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው ማረጋገጫ፣
7. እውቅና ካለው ላብራቶሪ ለምዝገባ የቀረበው ናሙና ምርመራ ውጤት

8. ለምርት ግብዓት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች እና የምግብ ጭማሪዎች ጥራት እና ደህንነት እንዲሁም ምንጫቸውን የሚያሳዩ ሰነዶች፣

9. የምርት የመጠቀሚያ ጊዜን ለመወሰን የተሰሩ ጥናቶች መረጃ፣

10. ለምዝገባ የቀረበው ምርት የእንስሳት ምርቶችና ተዋፆኦ ከሆነ ከእንስሳ ወደ ሰው ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት አግባብነት ካለው ተቋም ማቅረብ፣

11. ለምዝገባ የቀረበው ምርት ናሙና

12. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 11 ላይ የተቀመጠው የምርት ናሙና ገላጭ ፅሁፍ በጉልህ የተፃፈና የሚነበብ፣ የማይለቅ፣ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፈ ሆኖ፡-

ሀ) የምግቡን የንግድ ስም፤
ለ) የምግቡ የወል ስም፤
ሐ) በምግቡ ውስጥ ያለው የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት ዝርዝርና መጠን በሰንጠረዥ፤
መ) በምርት ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ የምግብ ግብዓት ስም ዝርዝር፤
ሠ) ምርቱ የተመረተበት ሀገርና የአምራች ወይም የአስመጪ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
ረ) የተመረተበት እና መጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን ፤
ሰ) የምርቱ መለያ ቁጥር ፤
ሸ) የምርቱ የተጣራ መጠን /ክብደት/፤
ቀ) ምርቱ የበለፀገ ምግብ ከሆነ የበለጸገበትን ንጥረ ነገር የሚያሳይ ግልፅ ፅሁፍ፤
በ) የተጨረረ ምግብ ከሆነ መጨረሩን የሚያሳይ ግልፅ ፅሁፍ፤
ተ) ምግቡ ልውጠ ህያው የሆኑ ግብዓቶችን በምርት ወቅት ከተጠቀመ ልውጠ ህያው መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣
ቸ) ለአለርጂክ የሚያጋልጡ ግብዓቶችን በምርት ወቅት ከተጠቀመ ይህንኑ የሚገልፅ መረጃ
ኘ) እንደ ምግቡ ባህሪ የአጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 (ረ) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ለትኩስ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች

ለ) የአልኮል መጠናቸው ከ10 በመቶ በላይ የሆኑ መጠጦች

ሐ) የተለያዩ ኮሚጣጤዎች

መ) ስኳር

ሠ) የስኳር መጠናቸው ከ 35 በመቶ በላይ የሆኑ ከረሜላዎች

ረ) ማስቲካዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው የምግብ አይነቶች ምርቶቹ ከታሸጉበት ወይም ከተመረቱበት ቀን ውጪ የመጠቀሚያ ጊዜ የማይጠየቅባቸው የምግብ አይነቶች ይሆናሉ፡፡

## 9. በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምግቦችን ስለመመዝገብ

ማንኛውም ዝርዝራቸው በዚህ መመሪያ ላይ አባሪ የተደረገ እና በሀገር ውስጥ የሚመረትና ለህብረተሰቡ የሚቀርብ ምግብ ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት በባለስልጣን መስሪያቤቱ ለማስመዝገብ ፡-

1. በዚህ መመሪያ ላይ በቅፅ ሁለት የተያያዘውን የተሞላ ቅፅ፤

2. ምግቡን ለማምረት በባለስልጣኑ የተሰጠው የቅድመ ምርት ፈቃድ፤

3. የምግቡ አምራች ድርጅት በባለሥልጣኑ እውቅና የተሰጠው የጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋታቸውን የሚያሳይ ምስክር ወረቀት፣

4. ለምርት ማምረት እንደ ግብዓት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች እና የምግብ ጭማሪዎች ጥራት እና ደህንነት እንዲሁም ምንጫቸውን የሚሳዩ ሰነዶች፣

5. የምርት የመጠቀሚያ ጊዜን ለመወሰን የተሰሩ ጥናቶች መረጃ፣

6. አስገዳጅ የደረጃን ምልክት ለመጠቀም ከሶስተኛ ወገን ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሰርተፊኬት፣

7. እውቅና ካለው ላብራቶሪ ለምዝገባ የቀረበው የምርት ናሙና ምርመራ ውጤት፤

8. ለምዝገባ የቀረበው የምርት ናሙና፤

9. በዚህ አንቀጽ ንኡሰ አንቀጽ 8 ላይ የተቀመጠው የምርት ናሙና ገላጭ ፅሁፍ በጉልህ የተፃፈና ሚነበብ፣ የማይለቅ፣ በአማርኛ ወይም በኢንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈ ሆኖ፡-

ሀ) የምግቡን የንግድ ስም፤
ለ) የምግቡ የወል ስም፣
ሐ) በምግቡ ውስጥ ያለው የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን በሰንጠረዥ፣
መ) በምርት ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ የምግብ ግብዓት ስም ዝርዝር
ሠ) ምርቱ የተመረተበት ሀገርና የአምራች ወይም የአስመጪ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
ረ) የተመረተበት እና መጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን ፤
ሰ) የምርቱ መለያ ቁጥር ፤
ሸ) የምርቱ የተጣራ መጠን /ክብደት/፤
ቀ) በባለሥልጣኑ የተሰጠውን የምዝገባ ቁጥር፤
በ) አስገዳጅ ሀገራዊ ደረጃ ምልክት፤
ተ) ምርቱ የበለፀገ ምግብ ከሆነ የበለጸገበትን ንጥረ ነገር የሚያሳይ ግልፅ ፅሁፍ፤
ቸ) ምግቡ የተጨረረ ምግብ ከሆነ መጨረሩን የሚያሳይ ፅሁፍ፤
ኀ) ምግቡ ልውጠ ህያው የሆኑ ግብዓቶችን በምርት ወቅት ከተጠቀመ ልውጠ ህያው መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣
ነ) ለአለርጂክ የሚያጋልጡ ግብዓቶችን በምርት ወቅት ከተጠቀመ ይህንኑ የሚገልፅ መረጃ
ኘ) እንደ ምግቡ ባህሪ የአጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ፤ የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 (ረ) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ለትኩስ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች

ለ) የአልኮል መጠናቸው ከ10 በመቶ በላይ የሆኑ መጠጦች

ሐ) የተለያዩ ኮሚጣጤዎች

መ) ስኳር

ሠ) የስኳር መጠናቸው ከ35 በመቶ በላይ የሆኑ ከረሜላዎች

ረ) ማስቲካዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው የምግብ አይነቶች ምርቶቹ ከታሸጉበት ወይም ከተመረቱበት ቀን ውጪ የመጠቀሚያ ጊዜ የማይጠየቅባቸው የምግብ አይነቶች ይሆናሉ፡፡

## 10. ስለ ቅድመ ማሳወቅ

ዝርዝራቸው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ያልተደረጉ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ ተመርተው ለህረተሰቡ ሽያጭ የሚቀርቡ የምግብ አይነቶች አስመጪ ወይም አምራች ምግቡን ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባቱ ወይም ለሽያጭ ከማቅረቡ አስቀድሞ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ለገቢ ምግብ በቅፅ 1 እና ለሀገር ውስጥ አምራቾች በቅፅ 2 መሰረት መረጃዎችን በትክክል በመሙላት ለባለሰልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 11. የምዝገባ ለውጥ፣ ዳግም ምዝገባና እድሳት ሁኔታ

1. ማንኛውም የተመዘገበ ምግብ በምርቱ ይዘትና ማሸጊያ ላይ ለውጥ ካልተደረገበት በስተቀር በየአራት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

2. የምግብ ምዝገባ ሰርተፊኬት ሲበላሽ፣ ሲጠፋ ወይም በተለያየ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ሲሆን ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ሊቀየርለት ይችላል፡፡

3. በምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ እንደ የማምረቻ ቦታ ፣ የማምረቻ መሳሪያ ፣ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ፣ የምርት ማሸጊያ አይነት ፣ የምርት ፎረሙሌሽን፣ የአመራረት፣ የምርት የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የምርት ስፔሲፊኬሽን እና ሌሎች ተመሳሳይ ከፍተኛ ለውጦች ሲኖሩ ምርቱን እንደገና ለማስመዝገብ የለውጡን ምክንያት፣ የውስጥ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት ሰርተፊኬት፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ለመወሰን የተጠና ሪፖርት፣ የሶስተኛ ወገን ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣ ለውጥ የተደረገበት ለምዝገባ የቀረበው ናሙና በማቅረብ ከተቀመጠው መስፈርት አንጻር በመገምገም የምዝገባ ለውጥ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

4. በምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የማያሳድሩ  እንደ የምርት ተወካይ ፣ የምርት የንግድ ስም ፣ የምርት ማሸጊያ ፣ የምርት የተጣራ ክብደት እና ሌሎች ተመሳሳይ ለውጦች ሲኖሩ አመልካቹ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ብቻ የምርቱን የምዝገባ ለውጥ ማድረግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. ምግብ ስለ ማስተዋወቅ

ማንኛውም የተመዘገበ ምግብ መተዋወቅ ያለበት በ"ምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 33/2008" መሆን ይኖርበታል፡፡

### 13. ስለ አስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድ

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም የምግብ አምራች ወይም አስመጪ በባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ ቁጥር 10/2004 የተዘረዘሩት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላል፡፡

### 14. ቅሬታ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ስርዓት

1. በዚህ መመሪያ መሰረት እርምጃ ስለተወሰደበት ምርት ቅሬታ ያለው ሰው በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት

   በአንድ ወር ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን አጣርቶ በ 30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

### 15. ተፈጻሚት የማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ መመሪያ ድንጋገጌዎች ጋር የማይጣጣም ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ከዚህ ቀደም የብቃት ማረጋገጫ በመውሰድ በስራ ላይ ባሉ አምራቾችና አስመጪዎች ላይ የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 (3) እና 9 (9፣ ቀ) የተደነገጉት ድንጋጌዎች አፈፃጸም ባለሰልጣኑ እስከ ህዳር 30 /2010 ሊያዘገያቸው ይችላል፡፡

### 17.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ነሃሴ 1/2009 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የሁሉ ደነቀው

የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር

**ቅፅ- አንድ**

## ለገቢ ምግብ የምዝገባና ፍቃድ ማመልከቻ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 1. | **አመልካች** | |
| | 1.1. ሙሉ አድራሻ /ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. | |
| | 1.2. ሥም | |
| 2. | **የምግቡ አስመጪ/ተወካይ (importer/agent)** | |
| | 3.1. ሥም | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ /ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. | |
| | 3.3. የድርጅቱ ተወካይ ሥም | |
| 3. | **የምግቡ አምራች** | |
| | 4.1. ሥም | |
| | 4.2. ሙሉ አድራሻ /ሀገር፣ክልል፣ የአካባቢው ልዩ መጠሪያ፣ ስልክ ቁጥር፣ ድህረ ገፅ፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. | |
| | 4.3. የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| 4. | **የምግቡ ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምግቡ ስም (የወል፣ የንግድ ስም) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ መጠን | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ አይትና መጠን | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 4.7. የምርት የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን /በሰንጠረዥ የቀረበ /tabular form/ | |
| | 4.8. ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ይዘት ዝርዝር | |
| 5. | **የምርት ምዝገባና ፍቃድ ሁኔታ** | |
| | ምርቱ የተመዘገበበትና ፍቃድ ያገኘባቸው ሀገራት ስም ዝርዝር፣ ወደ ገበያ እንዳቀርብ የታገደባቸውና በጥራና ደህንነት ጉድለት ከገበያ እንዲሰበሰቡ የተደረገባቸው ሀገራት ስም ዝርዝር | |
| 6. | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |

<table>
<tr><td></td><td colspan="3">እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለው፡፡<br><br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br><br>ሥም፡ ____________________________________________<br><br>ፊርማ፡ __________________________________________<br><br>በድርጅቱ ውስጥ ያሎት ሃለፊነት፡ __________________________________<br><br>ቀን፡ _____________________________________________</td></tr>
<tr><td rowspan="3">7.</td><td colspan="3">ለቢሮ አገልግሎት ብቻ<br><br>በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ</td></tr>
<tr><td>ማምልከቻው የገባበት ቀን</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ማሳሰቢያ፡</td><td colspan="2"></td></tr>
</table>

**ቅጽ- 2**

## ለሀገር ውስጥ ምግብ ምዝገባና ፍቃድ ማመልከቻ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 1. | **አመልካች** | |
| | 1.1 ሙሉ አድራሻ፡ ክልል፣ ዞን/ክፍለ ከተማ፣ ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. | |
| | 1.2 የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| 2. | **የማመልከቻው አይነት**<br><br>አዲስ ☐ ዳግም ☐ የምዝገባ ለውጥ ☐ | |
| 3. | **የምግቡ አምራች** | |
| | 3.1 . ሥም፡ | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ /ክልልዞን/ክፍለ ከተማ/ወረዳ፣ የአካባቢው ልዩ መጠሪያ፣ የቤት ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር የቢሮ፣ሞባይል፣ ድህረ ገፅ ኢ-ሜይል ወዘተ. | |
| | 3.3. የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| 4. | **የምግቡ ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምግቡ ስም (የወል፣ የንግድ ስም) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ ክብደት | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ አይትና መጠን | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 5.7 የምርት የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን /በሰንጠረዥ የቀረበ /tabular form/ | |
| | 5.8 ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ይዘት ዝርዝር | |
| 6 | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |

<table>
<tr><td></td><td colspan="3">እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች  ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለው፡፡<br><br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br><br>ሥም፡ ___________________________<br><br>ፊርማ፡ ___________________________<br><br>በድርጅቱ ውስጥ ያሎት ሃለፊነት፡ ___________________<br><br>ቀን: ___________________________</td></tr>
<tr><td>7</td><td colspan="3">ለቢሮ አገልግሎት ብቻ<br><br>በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ</td></tr>
<tr><td></td><td>ማምልከቻው የገባበት ቀን</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>ማሳሰቢያ፡</td><td colspan="2"></td></tr>
</table>

**ቅጽ-3**

| Category of food products to be registered | Lists of General products under category | |
|---|---|---|
| | English | Amaharic |
| Product nature | 1. Milk and milk product | 1. ወተትና የወተት ውጤቶች |
| | 2. Meat and meat product | 2. ስጋ እና የስጋ ውጤቶች |
| | 3. Poultry products | 3. የዶሮ ስጋ እና የዶሮ ውጤቶች |
| | 4. Sea foods | 4. ዓሣ እና ሌሎች የባህር ምግቦች |
| | 5. Processed Vegetables | 5. የተቀነባበሩ አትክልቶችና የአትክልት ውጤቶች |
| | 6. Sliced fruit | 6. የተዘጋጁ ፍራፍሬዎች |
| | 7. Nuts and their products | 7. የኦቾሎኒ ውጤቶች |
| Vulnerability of end users of the food product | 8. Therapeutic foods | 8. ልዩ የምግብ ፍላጎት ሟሟያ ምግቦች (ከ2 ዓመት በላይ ለሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎች) |
| | 9. Cereal based complementary foods (for more than 2 yrs young children's) | 9. ተጨማሪ የታዳጊ ህፃናት ምግብ (ከ 3 አስከ 10 ዓመት ላሉ ህፃናት) |
| | 10. Confectionery | 10. ከረሜላ እና ጣፋጭ ምግቦች |
| | 11. Fats and oils | 11. የምግብ ዘይትና ቅባቶች |
| | 12. Processed Fruit | 12. የተቀነባበሩ ፍራፍሬዎች |
| | 13. Packed water | 13. የተሸጉ ውሃዎች |
| | 14. Soft drinks | 14. ለስላሳ መጠጦች |
| | 15. Beers | 15. ቢራዎች |
| Fortified food | 16. Iodized salt | 16. አዮዲን ያለው ጨው |
| | 17. Noodles | 17. ኖድልሶች |